# የጸገየ ወይን (ደብተራው) እናት ከህልፈታቸው በፊት ጽፈውት የተገኘ እንጉርጉሮ

ከዚህ በታች የቀረበው ሰነድ የጸገየ ወይን (ደብተራው) እናት እማሆይ በላይነሽ ቦካን በሕይወት እያሉ ስለልጃቸው ናፍቆታቸውን ለመወጣት በስንኝ ቋጠሮ ያንጉራጎሩበት ነው። ከህልፈታቸው በሁዋላም ከቤታቸው ተገኝቷል። ደብተራውን "አንቺ" እያሉ ይጠሩት እንደነበረም ይታወቃል። "ደብተራውና ሌሎችም ደብዛቸው የጠፋ የህዝብ ልጆች የት ደረሱ ብለን በጋራ እንጠይቅ!" ስንልም ናፍቆትን እንዳረገዙ ያለፉት እማሆይ እና ሌሎች ብዙ የኢትዮጵያ ወላጆች አደራ ከመቃብር እያስተጋባብን ነው። በግዕዝ የሚጀምረው ሙሉው የእማሆይ እንጉርጉሮም እነሆ፡



ድምጸ እግሪሁ ለዝናም፣

ሶ ዘይዘንም ዝናም፣

ጸገየ ወይን ወፈርየ ሮማን፣

ሰናይት ሰላማዊት አንተ ናፍቅራ በጽድቅ፣

ገሪማ ግሩም ገረምከኒ ብጹዕ አባ ገሪማ፣

ተጎናጸፍ ሰናይ የመልአክ አስኬማ።

ጸገየ ወይንዬ፣ የኔ የብቻዬ፣

ልፍታ ላገልድምሽ፣ እስቲ እንደ ሱሪዬ፣

በጆሮዬ ላርግሽ፣ እንደ ጉትቻዬ፣

ያለሽበት ሀገር ጸሐይ ነውወይ ደመና?

ዝናብ ነውወይ ደመና?፣

አልቅሼ፣ አልቅሼ፣ ዓይኔ ደም አፈራ፣

አንቺ ጽኝ፣ ጽኝ፣ እኔንም ያጽናኝ፣

ሴራ ቆረጡብን፣ እንዳንገናኝ!

የባሕር ቄጤማ፣ የምትመስይው፣

ዘም ዘም አልሽና፣ ጋራውን ዞርሽው።

እስቲ ጠይቁልኝ፣ ምናለ በሆዷ?!

"እማይ ደህና ሰንብች"፣ ሳትለኝ መሄዷ?

ቅኔ ጸመድጓ፣ እቤትሽ ያለው፣

ማን ሊሰራው ነው?

ማን ሊመረግደው?

ትተሽ የሄድሽው?!